# የ2025-26 የPPRA አመታዊ የመብቶች ማስታወቂያ

የተማሪ መብቶች ማሻሻያ (The Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA) በዳሰሳ ጥናቶች፣በግብይት እና በተወሰኑ የአካል ምርመራዎችን መረጃ መሰብሰብን በተመለከተ ለአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች መብቶችን የሚሰጥ የፌዴራል ህግ ነው።የሲያትል የትምህርት ቦርድ የPPRA መብቶች እና ግዴታዎችን የሚገልጽ ቦርድ ፖሊሲ ቁጥር 3232 አፅድቋል።ስለ PPRA ተጨማሪ መረጃ በwww.ed.gov ማግኘት ይቻላል።

PPRA ተማሪዎች የሚከተሉትን አስመልክቶ በየዳሰሳ ጥናት ከመጠየቃቸው በፊት ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲያውቁት ይፈልጋል:

1. የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጅ ፖለቲካዊ ግንኙነት ወይም እምነት፤
2. የተማሪው ወይም የተማሪው ቤተሰብ የአእምሮ ወይም የስነ-ልቦና ችግሮች፤
3. ፆታዊ ባህሪ ወይም አመለካከት፤
4. ሕገ-ወጥ፣ፀረ-ማህበራዊ፣ራስን መወንጀል፣ወይም መጥፎ ባህርይ፤
5. ቅርብ የቤተሰብ ግንኙነት ያላቸው የሌሎችን ወሳኝ ግምገማዎች፤
6. ህጋዊ እውቅና ካላቸው እንደ ከህግ ባለሙያዎች፣ከዶክተሮች ወይም ከሚኒስትሮች ጋር ያሉ ግንኙነቶች፤
7. ተማሪው ወይም የተማሪው ወላጅ ሃይማኖታዊ ተግባራት፣ዝምድናዎች ወይም እምነቶች፤ወይም
8. የፕሮግራም ብቁነትን ለመወሰን በህግ ከተደነገገው ውጪ ገቢ።

የPPRA መብታቸው ተጥሷል ብለው የሚያምኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወደሚከተለው ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ:

Family Policy Compliance Office
U.S. Department of Education
400 Maryland Avenue SW
Washington, D.C. 20202

ከተገለጹት ስምንቱ ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ ስለ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጥያቄዎችን ለሚጠይቁ የዳሰሳ ጥናቶች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ማስታወቂያ የመቀበል፣ሲጠይቁ የመመርመር እና ተማሪዎቻቸውን ከመሳተፍ እንዲወጡ እንዲመርጡ እድል ሊሰጣቸው ይችላል።

ከተጠየቁት ስምንቱ ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ለሚጠይቁ የዳሰሳ ጥናቶች እና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ዲፓርትመንት ለሚደገፉ የዳሰሳ ጥናቶች - ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪዎቻቸው በዳሰሳ ጥናቱ ከመሳተፋቸው በፊት ማስታወቂያ የመቀበል፣ሲጠይቁ የመመርመር እና ፈቃድ የመስጠት መብት አላቸው።

እነዚህ መብቶች ከወላጆች/አሳዳጊዎች ወደ 18 አመት የሆነ ሰው ወይም በክልሉ ህግ ከወላጆች ቁጥጥር ውጭ የሆነ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ይተላለፋሉ።

## በ2025-26 የትምህርት ዘመን የሚጠበቁ የዳሰሳ ጥናቶች

የወጣቶች ጤና የዳሰሳ ጥናት - ይህ የዳሰሳ ጥናት የህዝብ ትምህርት ጽ/ቤት ዋና ሃላፊ፣የጤና ጥበቃ ዲፓርትመንት፣የጤና ጥበቃ ባለስልጣን የስነምግባር ጤና እና ማገገሚያ ክፍል እና የመጠጥ እና የካናቢስ ቦርድ የትብብር ጥረት ነው።ይህ ስም የማይጠቅስ የዳሰሳ ጥናት  በመክር ወቅት ለ6ኛ፣8ኛ፣10ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ይሰጣል።ከሌሎች ርእሶች መካከል ስለ የእፅ ሱሰኝነት፣የአእምሮ ጤና እና የቅርብ የቤተሰብ ግንኙነቶች የሚመለክቱ ጥያቄዎችን ይጠይቃል።የዳሰሳ ጥናቱን ቀድመው ለማየት እና/ወይም ላለመውሰድ የተማሪዎን ዋና ጽሕፈት ቤት ያነጋግሩ።

የወጣቶች የስነምግባር ስጋት ዳሰሳ - ይህ አገር አቀፍ የዳሰሳ ጥናት በየበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማእከል (CDC) የሚደገፍ ነው። የዳሰሳ ጥናቱ ጥያቄዎች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ስለ የአእምሮ ጤና፣ጾታዊ ስነምግባር እና የአደንዛዥ እፅ አጠቃቀምን ጨምሮ ስለ የጤና ባህሪያትን ይጠይቃሉ። ይህ የዳሰሳ ጥናት የሚካሄደው በበልግ ወቅት ነው።የዳሰሳ ጥናቱን ቀድመው ለማየት እና/ወይም  ላለመውሰድ የተማሪዎን ዋና ጽሕፈት ቤት ያነጋግሩ።

የትምህርት ቤት ሁኔታዎች የዳሰሳ ጥናቶች- ይህ በዲስትሪክት ደረጃ የሚሰጥ የዳሰሳ ጥናት በዓመት ሁለት ጊዜ (በልግ/ጸደይ) ከ3-12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይሰጣል።ይዘቱ ከየተማሪ ደህንነት፣ከባህላዊ ምላሽ ሰጪ እና ፀረ-ዘረኝነት ተግባራት፣ከማህበራዊ ስሜታዊ ደህንነት፣ከፆታዊ ማንነት እና (ከ6-12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ብቻ) የፆታዊ ፅንባሌ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ይሸፍናል።ሁሉም የዳሰሳ ጥናት ምላሾች ስም-አልባ ናቸው እና በትምህርት ቤቶች እና በዲስትሪክት ውስጥ ከግብ እና ከመከላከል ጋር ለማስማማት ጥቅም ላይ ይውላሉ። የዳሰሳ ጥናቱን ቀድመው ለማየት እና/ወይም  ላለመውሰድ እባክዎ የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የጥናት ዲፓርትመንት ገጽ (research@seattleschools.org https://www.seattleschools.org/departments/rea/district- surveys/) ያነጋግሩ እና/ወይም ይጎብኙ።

እራስዎን ይፈትሹ - ስለ ግለሰባዊ የጤና ባህሪያት ፈጣን ግብረመልስ የሚሰጥ መጠይቅ ነው።ከሌሎች ርእሶች መካከል ስለ እፅ አጠቃቀም፣የአእምሮ ጤና እና ደህንነት ጥያቄዎች ይጠየቃሉ።መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በጥቅምት እና በግንቦት መካከል በዓመት አንድ ጊዜ ራስን ፈትሽ (Check Yourself) ለተማሪዎች ለመስጠት አቅደዋል። የዳሰሳ ጥናቱን ቀድመው ለማየት እና/ወይም ላለመውሰድየት/ቤትዎን የመከላከል እና ጣልቃገብነት ባለሙያ ያነጋግሩ።

የጥንካሬዎች እና የችግሮች መጠይቅ - ይህ አጭር ማህበራዊ እና ስሜታዊ መጠይቅ በትምህርት ቤት ነርሶች የትምህርት ስኬትን ለማሳካት እና የትምህርት እንቅፋቶችን ለመቀነስ እንደ መሳሪያ ይጠቀሙበታል።ስለ የአእምሮ ጤና እና ህገወጥ ባህሪ የተመለከቱ ጥያቄዎች ይጠየቃሉ።SDQ-በFEPP levy-በሚደገፉ ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች በመኸር/ክረምት ወቅት ይሰጣል። የዳሰሳ ጥናቱን ቀድመው ለማየት እና/ወይም ላለመውሰድ  የተማሪዎን ትምህርት ቤት ነርስ ያነጋግሩ።

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በ 2025-26 የትምህርት ዘመን በዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ዲፓርትመንት የሚደገፈውን የዳሰሳ ጥናት ስምንት የሚታወቁ ርዕሰ ጉዳዮች የያዙ ጥያቄዎችን እንደሚይዝ አያውቅም።